EARLY CHILDHOOD EDUCATOR
PAY EQUITY FUND

# ድጎማ ለማይከፍሉ አቅራቢዎች የFY24 ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻን ማጠናቀቅ

ጁላይ 2023

OSSE

WE ARE WASHINGTON DC
GOVERNMENT OF THE
DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# እንኳን ወደ የልጅ ኢድገት ተቋም መሪዎች በደህና መጡ!



# የዙም ተሳትፎ

ጥያቄዎችዎን የ Q&A feature (**የጥያቄና መልስ ምርጫን**) በመጠቀም ያስገቡ።

ቀድመው መውጣት ይፈልጋሉ? በማንኛውም ጊዜ **ከስብሰባ ይውጡ** የሚለውን አዝራርን ይጫኑ።





ወደ **መገልገያ ጽሁፎች** የሚወስዱ ተጨማሪ **መረጃዎች** እና **ማስፈንጠሪያዎች** እዚህ ይጋራሉ።

ምርጫዎ በሆነ ቋንቋ ስብሰባውን ያዳምጡ። **የአማርኛ** ወይም **የስፓኒሽ አስተርጓሚን** ለማግኘት እዚህ ይጫኑ።

# በቀጥታ የሚተላለፉ ጥያቄዎች እና መልሶች









ጥያቄዎን እዚህ ይጻፉ እና ያስገቡ የሚለውን ይጫኑ።

# የዛሬ ተናጋሪዎች ጋር ተዋወቁ

- **Hannah Matthews**፣ የፖሊሲ፣ እቅድ እና ምርምር ዳይሬክተር፣ OSSE
- **Tierra Washington**፣ የፕሮግራም አስተዳዳሪ፣ ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ





# አጀንዳ

1. የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ በጀት አመት 2024 (FY24) እንዴት እንደሚሰራ
2. ድጎማ ለማይከፍሉ አቅራቢዎች መርጦ የመግባት ሂደት
   - የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ አጭር መግለጫ
   - በቅድመ ትምህርት ፈቃድ መስጫ መሳሪያ ክፍል (DELLT) ውስጥ ማመልከቻውን ማግኘት
   - የማመልከቻ ማሳያ
3. Q&A
4. መዝጊያ እና ቀጣይ ደረጃዎች

# የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ

OSSE
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ

- በFY24፣ OSSE በልጅ እድገት ተቋም (CDF) የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር አማካኝነት ለቅድመ አስተማሪዎች ማካካሻን ለመጨመር የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፎችን በቀጥታ ለልጅ እድገት ተቋማት ያሰራጫል።
  - የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ከአሁን በኋላ በAidKit በኩል በቀጥታ ክፍያዎችን አያገኙም።
- ከ CDF የደመወዝ ክፍያ ገንዘብ ቀመር ገንዘቦችን ለመቀበል፣ የልጅ እድገት ተቋማት በOSSE ፍቃድ የተሰጣቸው እና ብቁ ለሆኑ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች፣ በሥራ መደብ እና በዲግሪ፣ በOSSE ለ FY24 የተቋቋመውን ዝቅተኛ ደመወዝ የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ደሞዞችን ለመክፈል መስማማት አለባቸው፣
- ለመሳተፍ የሚፈልጉ የልጅ እድገት ተቋማት በOSSE በተሰየመ ሂደት አማካኝነት ወደ ፕሮግራሙ መርጠው መግባት አለባቸው።
  - መሳተፍ አማራጭ ነው ግን በጣም የሚበረታታ ነው።

# የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ

- በጁን፣ OSSE በCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር እና በዝቅተኛ ደሞዝ ላይ ያተኮሩ ሁለት ምናባዊ የመረጃ ክፍለ ጊዜዎችን አዘጋጅቷል።
  - ጁን 7 ምናባዊ የመረጃ ክፍለ ጊዜ ቀረጻ (ኢስፓኖል | አማርኛ)
  - ጁን 10 ምናባዊ የመረጃ ክፍለ ጊዜ ቀረጻ (ኢስፓኖል | አማርኛ)
- የተቋም መሪዎች የCDF ደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማቶች እንዴት እንደሚሰሉ እና የሚፈቀዱ የገንዘብ ድጋፍ አጠቃቀሞችን በተመለከተ ለልጅ እድገት ተቋም መሪዎች በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች ላይ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

# ድጎማ ለማይከፍሉ አቅራቢዎች
# መርጦ የመግባት ሂደት

# ድጎማ ለማይከፍሉ አቅራቢዎች መርጦ የመግባት ሂደት

- በ FY24 በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ለመሳተፍ የሚፈልጉ የልጅ እድገት ተቋማት ወደ ፕሮግራሙ መርጠው መግባት አለባቸው።
- መርጦ ለመግባት፣ ድጎማ የማይከፍል አቅራቢ ከዚህ በታች ያሉትን ደረጃዎች ማጠናቀቅ አለበት።

| ደረጃ | |
|---|---|
| **ደረጃ 1** | የFY24 ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ማመልከቻ ሞልተው ማስገባት |
| **ደረጃ 2** | የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ አቅራቢ ስምምነት መሙላት። |

- ብዙ ተቋማት የሚሰሩ ከሆነ፣ ለእያንዳንዱ ጣቢያ ማመልከቻ መሙላት አያስፈልግዎትም። በማመልከቻ ውስጥ፣ በፕሮግራም ውስጥ እንዲሳተፉ የሚፈልጓቸውን እርሶ የሚሰሯቸውን ተቋማት መምረጥ ይችላሉ።

# ቁልፍ የማስረከቢያ ቀን ገደቦች

| የFY24 መርጠ የመግባት/ ማመልከቻ እና ስምምነት የማስረከቢያ ቀን ገደቦች<br>*ሁሉም ቀን ገደቦች 5 p.m. ላይ ናቸው ET | | | |
|---|---|---|---|
| ሩብ ዓመት | የአቅራቢ መርጠ የመግባት/ ማመልከቻ ቀን ገደብ | የአቅራቢ ስምምነት ቀን ገደብ | የክፍያ ስርጭት |
| ሩብ አመት አንድ | ሴፕቴምበር 15፣ 2023 | ሴፕቴምበር 30፣ 2023 | ዲሴምበር 2023 |
| ሩብ አመት ሁለት | ዲሴምበር 15፣ 2023 | ዲሴምበር 31፣ 2023 | ማርች 2024 |
| ሩብ አመት ሶስት | ማርች 15፣ 2024 | ማርች 31፣ 2024 | ጁን 2024 |
| ሩብ አመት አራት | ጁን 15፣ 2024 | ጁን 30፣ 2024 | ሴፕቴምበር 2024 |

# የማመልከቻ ማጠቃለያ



# FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ማመልከቻ

- ድጎማ ለማይከፍሉ አቅራቢዎች የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ማመልከቻን በDELLT ማግኘት ይቻላል።
- ማመልከቻው አራት ክፍሎች አሉት፡-

1. የስነ ህዝብ አወቃቀር መረጃን መገምገም እና ማረጋገጥ
2. ማረጋገጫዎችን ማንበብ እና እውቅና መስጠት
3. አስፈላጊ ሰነዶችን ማስገባት
4. በፕሮግራሙ ውስጥ ለመሳተፍ ተቋሙን ወይም ተቋሞቹን ይለዩ

# ደጋፊ ሰነዶች

- የሚከተሉትን የተሟሉ ሰነዶች ማቅረብ ይጠበቅብዎታል፦
  - የIRS የአሰሪ መለያ ቁጥር (EIN) የማረጋገጫ ደብዳቤ
  - የIRS ቅጽ W-9
  - የዲስትሪክት የተቀናጀ የፋይናንስ ስርዐት (DIFS) አቅራቢ የፈቃድ ሰነድ
- አቅራቢዎች አስፈላጊውን ሰነድ በተቻለ ፍጥነት እንዲሰበስቡ እና እንዲያሟሉ ይበረታታሉ።

# የIRS EIN የማረጋገጫ ደብዳቤ

- አቅራቢዎች የEIN ማረጋገጫ ደብዳቤያቸውን ቅጂ ማስገባት አለባቸው።
- ለስራዎ ከዚህ ቀደም አመልክተው EIN ከተቀበሉ፣ ነገር ግን ያለቦታው ካስቀመጡት፣ ከIRS የስራ እና ልዩ የግብር መስመር በ800-829-4933 ከሰኞ እስከ አርብ ከ7 a.m.–7 p.m በመደወል የእርስዎን EIN መጠየቅ ይችላሉ።

# IRS W-9 ቅጽ

- IRS ቅጽ W-9 ያውርዱ
- ትክክለኛውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ለማቅረብ ቅጹን ይሙሉ።

# የDIFS አቅራቢ የፈቃድ ሰነድ

- በ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ውስጥ ለመሳተፍ፣ አቅራቢው በዲሲ ዋና በፋይናንስ መኮንን (OCFO) የሚተዳደር፣ የዲስትሪክት መንግስት የፋይናንስ ስርዐት በሆነው በDIFS ውስጥ መመዝገብ አለበት።
- **በDIFS ውስጥ ለመመዝገብ እነዚህን መመሪያዎች ይከተሉ።**
- ስለ DIFS ምዝገባ ጥያቄዎች፣ ለOCFO በsuppliers@dc.gov ኢሜይል ያድርጉ ወይም ወደ (202) 442-6870 ከሰኞ እስከ አርብ በ8 a.m. እና 5 p.m. መካከል ባለው ሰአት ይደውሉ
- ተቋሙ በተሳካ ሁኔታ በ DIFS ውስጥ ከተመዘገበ በኋላ፣ ከ DIFS/OCFO የፈቃድ ኢሜይል ይደርስዎታል። የማጽደቂያ ማሳወቂያ ኢሜይል የPDF ቅጂን ያስቀምጡ። ይህ እንደ ስኬታማ የDIFS አቅራቢ ምዝገባ ማረጋገጫ መቅረብ አለበት።
- ማሳሰቢያ፥ አስቀድመው በDIFS ውስጥ ከተመዘገቡ፣ አዲስ መለያ አይፍጠሩ። በDIFS ውስጥ መመዝገብዎን ማረጋገጫ ለመጠየቅ እባክዎ OCFOን ያነጋግሩ። የ DIFS መለያ እንዳለዎት እርግጠኛ ካልሆኑ፣ እባክዎ OCFOን ያነጋግሩ።

# ማመልከቻውን በDELLT ውስጥ ማግኘት



EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

OSSE


GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# ማመልከቻውን ማግኘት


- **ማመለከቻው የሚሞላው በተቋሙ ህጋዊ ባለቤት/ኦፕሬተር ነው።**
  - የህጋዊው ባለቤት/ኦፕሬተር የእውቂያ መረጃ በDELLT ውስጥ ባለው የህግ ባለቤት/ኦፕሬተር መረጃ ክፍል ውስጥ ይገኛል።
  - ብዙ ተቋማት የሚሰሩ ከሆነ፣ ለእያንዳንዱ ጣቢያ ማመልከቻ መሙላት አያስፈልግዎትም። በማመልከቻ ውስጥ፣ በፕሮግራም ውስጥ እንዲሳተፉ የሚፈልጓቸውን እርሶ የሚሰሯቸውን ተቋማት መምረጥ ይችላሉ።
- ማመለከቻውን ለማግኘት፣ የአቅራቢው መግለጫ በ DELLT ውስጥ በህጋዊው ባለቤት/ኦፕሬተር ገቢር መሆን አለበት።
- በ DELLT ውስጥ ያለው የእያንዳንዱ ተቋም ህጋዊ ባለቤት/ኦፕሬተር የአቅራቢውን መግለጫ ለማግበር ጠቅ ማድረግ ያለበት ማስፈንጠሪያ ከQuickBase ኢሜይል ተልኳል።

# ማመልከቻውን ማግኘት

- ከ notify@quickbase.com “የማመልከቻው ግብዣ” በሚል ርዕስ የተላከ ኢሜይል ይፈልጉ
- የኢሜይሉ አካል በቀኝ በኩል ያለውን ምስል ይመስላል።
- **“ወደዚህ ማመልከቻ በ QUICKBASE ይሂዱ"** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ
- እንደ ህጋዊ ባለቤት/ኦፕሬተር ከተዘረዘሩ እና ኢሜይሉን ማግኘት ካልቻሉ፣ እባክዎ የአይፈለጌ መልዕክት/ አይፈለጌ ማህደርዎን ያጣሩ። ኢሜይሉ ከሌለ፣ OSSE.ECEPayEquity@dc.govን ያነጋግሩ።



# ማሳያ፦ ማመልከቻ እና የመልዕክት መላላኪያ ባህሪያት




# ድጋፍ ያግኙ

- ድጎማ ለማይከፍሉ አቅራቢዎች የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ማመልከቻ መመሪያዎችን ይገምግሙ።
- የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ማመልከቻን ለመሙላት ጥያቄዎች ያላቸው ወይም ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ድጎማ የማይከፍሉ አቅራቢዎች የመልዕክት መላላኪያ ባህሪን በ DELLT ውስጥ እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።
- ከድጋፍ ባለሙያ ጋር ለመገናኘት አቅራቢዎች ለOSSE.ECEPayEquity@dc.gov ኢሜይል መላክ ይችላሉ።

# Q&A

# ተቋምዎ በ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ለመሳተፍ አቅዷል?

እባክዎ በማያ ላይ ለዙም ምርጫ ምላሽ ይስጡ



# መዝገቢያ እና ቀጣይ ደረጃዎች

# ቁልፍ የማስረከቢያ ቀነ ገደቦች

| የFY24 መርጦ የመግባት/ ማመልከቻ እና ስምምነት የማስረከቢያ ቀነ ገደቦች<br>*ሁሉም ቀነ ገደቦች 5 p.m. ላይ ናቸው ET | | | |
|---|---|---|---|
| ሩብ ዓመት | የአቅራቢ መርጦ የመግባት/ ማመልከቻ ቀነ ገደብ | የአቅራቢ ስምምነት ቀነ ገደብ | የክፍያ ስርጭት |
| ሩብ አመት አንድ | ሴፕቴምበር 15፣ 2023 | ሴፕቴምበር 30፣ 2023 | ዲሴምበር 2023 |
| ሩብ አመት ሁለት | ዲሴምበር 15፣ 2023 | ዲሴምበር 31፣ 2023 | ማርች 2024 |
| ሩብ አመት ሶስት | ማርች 15፣ 2024 | ማርች 31፣ 2024 | ጁን 2024 |
| ሩብ አመት አራት | ጁን 15፣ 2024 | ጁን 30፣ 2024 | ሴፕቴምበር 2024 |

በ FY24 የቅድመ ልጅነት ትምህርት ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን የሚከተለውን ይጎብኙ፦ osse.dc.gov/fy24ecepayequity

የመገልገያ ጽሁፎች፥

- FY24 CDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር
- የFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች እና የደመወዝ መርሃ ግብር
- በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች
- ለድጎማ ለማይከፍሉ አቅራቢዎች የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻን ለመሙላት መመሪያ

ለጥያቄዎች እና ለድጋፍ፣ እባክዎ በOSSE.ECEPayEquity@dc.gov ኢሜይል ይላኩ።

# የዛሬውን የመረጃ ክፍለ-ጊዜ ስለተካፈሉ እናመሰግናለን!

EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR